# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 24 ኛ ሳምንት

## ገብርኄር

### የትምህርቱ ዓለማ

- እግዚአብሔር በሰጠን ታማኝ ስለመሆን መማር።

### መግቢያ

- ልጆች ከነገ ጀምሮ ያለው ሳምንት በቤተክርስቲያን ገብርኄር የሚባለው የዐቢይ ጾም 6ኛ ሳምንት ነው።
- ገብርኄር ማለትም 'ታማኝ አገልጋይ' ማለት ነው። በዛሬው ትምህታችንም በዚህ ላይ በመመርኮዝ በሕይወታችን እግዚአብሔር በሠጠን ነገር ሁሉ ታምነን የተሻለ ሥራ ስለመስራት እንማራለን።

### የትምህርቱ ይዘት

- ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25÷1-ፍጻሜ ምዕራፍ ስለ ምጽአቱ ሲያስተምር ሦስት ምሳሌዎችን ገልጾል።
  1. 10ሩ ደናግል
  2. የባለ መክሊቱ ነጋዴ /ገብርኄር እና ገብር ሐካይ/
  3. የበግና የፍየል ምሳሌ።
- ከእነዚህም ስለ ባለ መክሊቱ ነጋዴ ያስተማረውን በዛሬው ትምህርታችን እናያለን።
- አንድ ባለጠጋ ወደ ሌላ ሊሄድ ፈለገና ባሮቹን ጠርቶ ያለውን ገንዘብ እንደ የአቅማቸው ሠጣቸው፡- ለአንደ አምስት ለሁለተኛውም ሁለት ለሦስተኛውም አንድ መክሊት ሠጣና ወደ ሌላ ሀገር ሄደ።
- ባለ 5 (አምስት) መክሊት ወጥቶ ወርዶ አምስት መክሊት አተረፈበትና አሥር አደረገው። ሁለት የተቀበረውም አራት አደረገው። አንድ የተቀበለው ግን ቆፍሮ ቀበረው።
- ከብዙ ዘመንም በኂላ ባለጠጋው ሰው መጥቶ ተቆጣጠራቸው፡-
  - ባለ 5ቱ አምስት ሠጠኸኝ አትርፌ አሥር አደረኩት ባለሁለቱም አራት አደረኩት አሉ።
  - አንድ መክሊት የተቀበለውም የሰጠኸኝን በምድር ቀበሬ አስቀምጨው ነበር እነሆ ብሎ አሰረከበ።
- ጌታቸውም ሁለቱን በብዙ ስለታመኑ ወደ ጌታቸው ደስታ እንዲገቡ ሲሾማቸው።ባለ አንድ መክሊቱንም የተረከበውን አላተረፈም ነበርና ወደ ውጭ አውጥተው እንዲጥሉት አዘዘ።
- ልጆች ከዚህ ምሳሌያዊ ታሪክ 'ገብርኄር' እንደተባሉት ታማኝ አገልጋዮች እኛም እግዚአብሔር በሠጠን ነገር በማስተዋልና በትጋት ውጤታሞች እንድንሆን ይፈልጋል።
  - በትምህርታችን ጎበዝና አጥኚዎች እንጂ ሠነፎች መሆን የለብንም።
  - የተማርነውን በመተግበርም ቤተሰቦቻችን ታማኞች፣ ጎበዞች፣ ውጤታማዎችም ብለው የሚያመሰግኑን መሆን አለብን።
  - በ40 እና በ80 ቀናችን ስንጠመቅ እግዚአብሔር የሠጠን የተለያዩ የጸጋ ስጦታዎች ስላለንም በቤተሰቦቻችን ምክር እና ቤተክርስቲያን በምንማረው መሠረት ተሰጥኦችንን ማሳደግ ጠንካሮች መሆንም ይገባናል።

### መዝሙር

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ይጠብቀኛል
በእረፍት ውሃ በለምለም መስክ (2) እኔ ይመራኛል።

**ይቆየን፡፡**